# ግጥም በያይነቱ

በዘውገ ፋንታ

ነሐሴ 2010

ደሴ ይብቃህ ተነስ፣
እምቢ! አለ አድዋ፣
ጎጃም ቶሎ ድረስ፣
ፍቼ ገብቷል ሸዋ።

ሐማሴን ና ውረድ፣
ተከዜም ቢሞላ፣
በጎንደሩ መንገድ፣
ተሻገር በመላ።

ባድሜ ቅበር ዘመድ፣
አሰብን ጨው በላ፣
ተከዜ ይታገድ፣
ከዚያ ውሃ ይፍላ፣
ከላይ አለ ጉድ፣
ይመጣል በኋላ።

ቤት እንስራ አልጋ፣
አሁን እናመቻች፣
ጠጋ በል ወለጋ፣

ሀረርጌ ገጥማለች፣

ባሌን ፈልጋ፣

አሩሲን አቅፋለች።

ኢሊባቡር ይምጣ፣

ገሙጎፋን ይዞ፣

ሲዳሞ ካልወጣ፣

ምን ይዞ ጉዞ!

ሁሉም የኛ ዕጣ፣

ይድረስ ተያይዞ፣

ተቃቅፎ ይምጣ፣

ወገን ተጋግዞ፣

ታስወርድ ያውጣ፣

እንግዳን ልጅ መዞ፣

ኢትዮጵያ አትቆጣ፣

በዚች ትንሽ ጣጣ።

በሉ ወሎ መጀን!

አወሉ ደርሶናል፣

በረካ ከጠጣን፣

መንገዱ ይቀናል።

ጥጋብ ነው ርሃብ፣

የበላው ያልቅስ፣

ክተት! በል በደቡብ፣

አይቅር አንድ ነፍስ፣

ይግባ ይመዝገብ፣

የሰሜኑም ይድረስ፣

ያለው በምዕራብ፣

የወጣው ይመለስ።